## ምዕራፍ ፮

### ዘጥምቀት ምንባብ

፩ በስመ እግዚአብሔር በከመ ሥርዓተ ናዝራውያን ዘንሜልሶ። ወበከመ ቃለ ሱራፌል ዘንቄድሶ፡ ውስተ ጽርሐ አርያም ዘአንበረ አትሮንሶ። እደ ሰብእ ኀበ ኢይገስሶ፡ኀሊና መዋቲ ኀበ ኢየኀሥሦ፡፡ዲበ አርእስተ አድባር ለተነ ጊሜ ዘያጠይሶ፡ እንበለ ረዓም ዘያግሕሦ፡ ውስተ አየራት ዘያስተቃልሶ፡ ወለገጸ ሰማይ ርጊብ አጽፈ ደመና ዘያለብሶ፡፡ዘሎቱ ይደሉ ስብሐት ወተወድሶ፡ ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

፪ ንበልኬ ዘለፋሁ ለአርጌንስ ዘይቤ ኢይክል ይርአዮ ወልድ ለአብ በእንተ ዕበይ ዘሀሉ ላዕሌሁ ለአብ፡ወኢይክል ይርአዮ መንፈስ ቅዱስ ለወልድ በእንተ ዕበይ ዘላዕሌሁ ለወልድ፡ ኢይክሉ ይርአይዎ መላእክት ለመንፈስቅዱስ በእንተ ዕበይ ዘላዕሌሁ ለመንፈስቅዱስ፡ ኢይክሉ ውሉደ ሰብእ ይርአይዎሙ ለመላእክተ ሰማይ በእንተ ዕበይ ዘላዕሌሆሙ ለመላእክተ ሰማይ ፡፡ ገብረ ሎቱ መዓርገ ፭ ወኢይነጽርዎ፡፡

፫ አርጌንስሰ ሀዋኪ በግዕዙ ወጽል ሕው በልሳኑ፡፡ መፍቀሬ ዘውዕ ዘራኤ ነቢብ፡ ዕቡየ ዓይን ወንፉሐ ልብ፡ ይዘሩ ሀከከ በአብያተ ክርስቲያናት ዘእስክንድርያ ወይዘርእ አስዋከ በአ ድያመ ግብጽ፡፡ይሜህር ፍሉጠ እምኤጲስቆጶ ሳት ወኢይዴቅስ እመ ኢገብራ ለእኪት፡፡ወአስተ ርእዮቱሰ ምስለ አርዮስ ንፉቅ ወምስለ ሚሊጢስ ፈታዊ ሢመት፡፡

፬ አርዮስ ዘረዋ ለቤተክርስቲያን እንበይነ ኑፋቄሁ እንዘ ይሰድዶሙ ለመሀ ይምናን በረድኤተ ንጉሥ፡፡ ወእምድኅረዝ ቆመት ርቱዐ እመ ጉባኤሆሙ ለ፫፻፲ወ፰ እለ አማኅበሩ በኒቅያ በመዋዕለ ቈስጠንጢኖስ ርቱዐ ሃይማ ኖት፡፡ ሚሊጢስ ደበያ ለቤተክርስቲያን በመሢጠ ጽጽስናሁ ለጴጥሮስ፡፡ ወዘለፋሁሰ አኮ በበይነ ሃይማኖት አላ በፈቲወ ሢመት፡፡ወአርጌንስሰ በገ ቢረ ሀከክኒ ወበወልጦ ሃይማኖትኒ እስመ ይሜ ሀር ተኀጻጸ ወልድ እምአብ ወተኀጻጸ መንፈስ ቅዱስ እምወልድ ፡፡

፭ እፎኬ ይቤ አርጌንስ የሐጽጽ ወልድ እምአብ፡፡ገብረ ሎቱ ምክንያተ እምቃለ ወንጌል ዘይቤ ሶበሰ ታፈቅሩኒ እምተፈሣሕክ ሙኒ ብየ እስመ አነ አሐውር ኀበ አብ እስመ ውእቱ አብ የዐብየኒ፡፡እፎኬ የዐብዮ አብ ለወልድ ዘኢቀደሞ ሰዓተ ወኢዕለተ ኢከመ ቅጽበተ ዓይን ወኢከመ ጥፍሐተ አክናፈ ንስር፡እስመ አብ የዐ ብየኒ ዘይቤ አማንኬ የዐብዮ መለኮት ለትስብእት እስከ አመ ነበረ በየማነ አቡሁ፡፡ ወእምድኅረሰ

## ምዕራፍ ስድስት

### የጥምቀት ምንባብ

፩ እንደ ናዝራውያን ሥርዓት በሦስትነት በምናመሰግነው እንደ ሱራፌልም ቃል በምናመ ሰግነው የሰው እጅ በማይነካው የሚችም ኀሊና በማይመረምረው በጽርሐ አርያም አትሮንሱን ያኖረ በተራሮች ራስ ላይ የጉምን ተን በሚያተን ያለጩኸት የሚያስወግደው በአየራት ውስጥ በሚያመላልሰው ሰፊውን የሰማይ ገጽ የደመና ግምጃን በሚያላብሰው በእግዚአብሔር ስም ክብ ርና መመስገን የሚገባው ለዘላለሙ አሜን፡፡

፪ በአብ ላይ ባለ ጌትነት ምክንያት ወልድ አብን ያየው ዘንድ አይችልም መንፈስቅዱስም በወልድ ላይ ባለ ጌትነት ምክንያት ወልድን ሊያየው አይችልም በመንፈስቅዱስ ዘንድ ባለ ጌትነት ምክንያት መላእክት መንፈስ ቅዱስን ሊያዩት አይቻላቸውም በሰማይ ላይ ስላለ ክብር የሰው ልጆች የሰማይ መላእክትን ያዩአቸው ዘንድ አይችሉም ያለ የአርጌንስን ተግሣጽ እንናገር አምስት መዓርጋትን አደረገለት አላዩ ትምም፡፡

፫ አርጌንስስ በጠባዩ የሚያውክ በአንደበቱም የሚሸነግል ጨዋታ የሚወድ ተናጋሪ በዓይኑ የሚታበይ ልቡም ያበጠ በእስክንድርያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ክርክርን ይበትናል በግ ብጽ አውራጃዎችም እሾህን ይዘራልከ፣ኤጲስቆጶሳት የተለየውን ያስተምራል ክፋትንም ካላደረጋት አያንቀላፋም፡፡መነሣቱም ከተጠራጣሪው ከአር ዮስ ሹመትንም ከሚሻ ከሚሊስጢስ ጋር ነው፡፡

፬ አርዮስ ስለክህደቱ ምእመናንን በንጉሥ ርዳታ እያሳደዳቸው ቤተ ክርስቲያንን በተናት፡፡ ከዚህም በኋላ ሃይማኖቱ በቀና በቈስጠንጢኖስ ዘመን በኒቅያ በተሰበሰቡ በሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ጉባኤ ጊዜ ቀጥ ብላ ቆመች፡፡ሚሊጢስ የጴጥሮስን ጵጵስና በመንጠቅ ቤተ ክርስቲያንን በዘበዛት፡ ዘለፋው ስለሃይማኖት ጉዳይ አይደለም ሹመትን በመሻት እንጂ፡፡ አርጌንስ ግን ክርክር በመፍጠር ሃይማኖትንም በመለወጥ ነው፡፡ የወልድን ከአብ ማነሥ የመንፈስ ቅዱስንም ከወልድ ማነስ ያስተምራልና፡፡

፭ አርጌንስ እንደምን ወልድ ከአብ ያንሣል አለ፡፡ ብትወዱኝስ በእኔ ደስ በተሰኛችሁ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁ አብ እርሱ ይበልጠኛልና ያለውን ከወንጌል ቃል ምክንያት አደረገለት፡ አብ የሰዓትና የቀንን የዓይን ጥቅሻና የንስር ክንፎች መማታትን ያህል ያልቀደመውን ወልድን እንደ ምን ይበልጠዋል፡፡አብ ይበልጠኛል ያለው በእው ነት መለኮት ሰብእናን ይበልጠዋል፡፡በአባቱ ቀኝ እስከ ተቀመጠበት ጊዜ ድረስ፡በአባቱ ቀኝ ከተቀ መጠ በኋላ ግን አብ ይበልጠኛልና አላለም፡፡ ዳግ

ነበረ በየማነ አቡሁ ኢይቤ እስመ አብ የዐብየኒ:: ወዓዲ ይቤ አዐርግ ሰማየ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ ኀበ አምላኪየ ወአምላክክሙ::ወዘይቤሰ እምቅድመ ዕርገቱ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ ኀበ አምላኪየ ወአምላክክሙ እንዘ ያርኢ ትሕትና ዘፍና ትስብእት::አቡሆሙ ሎሙ በጸጋ ወሎቱሰ በአማን፡ አምላኮሙ ሎሙ በአማን ወሎቱሰ እንበይነ ሥጋዌሁ::ወእምድኅረ ዕርገቱሰ ኮነ ዕሩየ ትስብእቱ ምስለ መለኮቱ::ተፈጸመ ቃለ እግዚአብሔር ዘይቤ በኦሪት አዳም ኮነ ከመ ፩ እምኔነ:: ዘፍ፫+፳፪ ዮሐ፲፮+፯፣፳+፲፯

፮ ወበእንተ ዕሪና አብ ወወልድ ይቤ እግዚእነ በወንጌል አነ ወአብ ፩ ንሕነ:: ወካዕበ ሰማዕ ዘከመ ይቤሎ ፊልጶስ ለእግዚእነ አርእየናሁ ለአብ ወየአክለነ::ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ዘርእየ ኪያየ ርእዮ ለአቡየ:: ወዓዲመ ይቤ አነ በአብ ወአብ ብየ:: ወዓዲመ ይቤ ሰብሐኒ አባ በስብሐቲከ ዘሀሎ ምስሌከ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም:: ወመጽአ ቃል እምሰማይ ዘይብል ሰባሕኩከሂ ወዓዲ እሴብሐከ:: ዮሐ ፲፯+፭

፯ አእምርኬ ኦ አርጌንስ ከመ ተሰብሐ ወልድ እምኀበ አቡሁ:: ወእመሰኬ አቡሁ ሰብሖ እፎኬ ትብሎ የሐጽጽ::አኮኬ ይረክቦ ተኀጻጽ ለወልድ እምአቡሁ አላ አንተ ትከውን ኀጹጸ እም ዐቢየ ክርስቲያን:: ወበእንተ መንፈስቅዱስኒ ትትሔዘብኑ ከመ የሐጽጽ እምወልድ::

፰ ስማዕ ዘይቤ በወንገል ወሶበ መጽአ ጰራቅሊጦስ ዘእፌኑ ለክሙ አነ እምኀበ አብ መንፈሰ ጽድቅ ዘይወጽእ እምኀበ አብ ውእቱ ሰማዕትየ:ወአንትሙሂ ሰማዕትየ ከመ እምትካት ሀሎ ምስሌየ::ወበዝኒ ኢትሌቡኑ ሶበ ይብለከ ይወጽእ እምኀበ አብ::ወእመሰ ይወጽእ እምኀቤሁ እፎኬ እንከ ኢይሬእዮ::ወመትልዎ ይብል ወአንትሙሂ ሰማዕትየ ከመ እምትካት ሀሎ ምስሌየ::ወእመሰ እምትካት ሀሎ ምስሌሁ እፎኬ ኢይሬእዮ ወእፎኑ የሐጽጽ እምኔሁ:: ዮሐ ፲፭+፳፮

፱ ጳውሎስኒ ይቤ ወአልቦ ዘየአምር ኅሊናሁ ለእግዚአብሔር ወመኑ መማክርቲሁ :: ንሕነሰኬ ኅሊናሁ ለክርስቶስ ብነ::ወአነሂ አኃዊነ ስእንኩ ምህሮተክሙ ከመ ዘመንፈስቅዱስ ኅሊናሁ ለክርስቶስ::ወእመሰ ኅሊናሁ ለክርስቶስ ውእቱ እፎኬ ኢይሬእዮ እስመ ኅሊና የዐቢ እምነጽሮ ገጽ ወፈቲነ አልባብ የዐቢ እምርእየ አፍአ:: ወካዕበ ይቤ ጳውሎስ አልቦ ዘየአምር ኅሊናሁ ለብእሲ ዘእንበለ መንፈሱ ለብእሲ ዘላዕሌሁ::ንሕነሰኬ ኅሊናሁ ለእግዚአብሔር ብነ ዘይፈትን ኅቡአቲሁ ወይከሥት ማዕምቅቲሁ:: ፩ቆሮ፪+፲፮

፲ አእምርኬ ኦ አብድ ከመ ወልድኒ ይሬእዮ ለአብ:: በከመ ይቤ በወንጌል ኢይክል

መኛም ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ አለ:: ከዕርገቱ በፊት ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ያለው ለሰውነት የሚገባ ትሕትናን እያሳየ ነው::ለእነርሱ በጸጋ አባታቸው ነው ለርሱ ግን በእውነት አባቱ ነውና:: ለእነርሱ በእውነት አምላካቸው ነው ለርሱ ግን ሰው ስለመሆኑ ነው:: ከዕርገቱ በኋላ ግን አዳም ከእኛ እንደ አንዳችን ሆነ ያለው ሰውነቱ ከመለኮት ጋር የተካከለ ሆነ በኦሪት የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ተፈጸመ::

፮ ስለ አብና ስለወልድ እኩልነት ጌታችን በወንጌል እኔና አብ አንድ ነን አለ:: ሁለተኛም ፊልጶስን ጌታችንን አብን አሳየንና ይበ ቃናል እንዳለው ስማ::ጌታ ኢየሱስም እኔን ያየ አባቴን አይቶታል አለው:: እንደገናም እኔ በአብ አለሁ አብም በእኔ አለ አለ::ዳግመኛም አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር አስቀድሞ ከአንተ ጋር በነበረኝ ክብር አክብረኝ አለ::ከሰማይም አከበርሁህ ገናም አከብርሀለሁ የሚል ቃል መጣ::ዮሐ ፲፯+፭

፯ አርጌንስ ሆይ ወልድ ከአባቱ ዘንድ እንደከበረ ዕወቅ አባቱ ካከበረው እንደምን ያንሣል ትለዋለህ ወልድን ከአባቱ ዘንድ ማነስ የሚያገኘው አይደለም አንተ ከክርስቲያን ታላላቆች የምታንስ ትሆናለህ እንጂ::

፰ በወንጌል ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ ከአብ የሠረፀ አጽናኙ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል እናንተም ከቀድሞ ጀምሮ ከእኔ ጋር እንዳለ ምስክሮቼ ናችሁ ያለውን ስማ:: በዚህም ከአብ ይወጣል ሲል አታስተውልምን ከእርሱ ዘንድ የሚወጣ ከሆነ እንግዲህ እንዴት አያየውም::ተከታዩም እናንተም ከቀድሞ ጀምሮ ከእኔ ጋር እንዳለ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል ከቀድሞ ጀምሮ ከእርሱ ጋር ካለ እንዴት አያየውም እንዴትስ ከእርሱ የንሣል:: ዮሐ ፲፭+፳፮

፱ ጳውሎስም የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ የለም ያማከሩት እነማን ናቸው አለ፡ እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን ወንድሞቼ ሆይ እኔም መንፈስቅዱስ በርሱ እንዳለ ሰው እናንተን ማስተማር ተሳነኝ አለ:: እነሆ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን የክርስቶስ ልብ አለው፡ የክርስቶስ ልብ ከሆነ እንደምን አያየውም ኅሊና ፊትን ከማየት ልብን መመርመርም የውጪውን ከማየት ይበልጣልና:: ሁለተኛም ጳውሎስ በእርሱ ላይ ካለው የሰው መንፈስ በቀር የሰውን አሳብ የሚያወቅ የለም እኛ ግን የተሸሸገውን የሚመረምር ጥልቆችንም የሚገልጥ የእግዚአብሔር ልብ አለን:: ፩ቆሮ፪+፲፮

፲ አንተ ሰነፍ በወንጌል ከአብ ያየውን ካልሆነ በቀር ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ

ገቢረ ወልድ ዘእምኀቤሁ ወኢምንትኒ ዘእንበለ ዘርእዮ ለአብ ይገብር ዘውእቱ ገብረ ከማሁ ወልድኒ ይገብር በአምሳሉ:: እስመ አብ ያፈቅር ወልዶ ወኵሎ ያሬእዮ ዘውእቱ ይገብር ወዘየዐቢ እምዝ ያሬእዮ ግብረ ከመ አንትሙ ታእምሩ ወታንክሩ:በእንተ መንፈስቅዱስኒ ቀዲሙ ነገርና ከሙ እምይእዜሰ ኢትበሉ ኦ ረሲዓን የሐጽጽ ወልድ እምአብ ወኢይሬእዮ::ወየሐጽጽ መንፈስ ቅዱስ እምወልድ ወኢይሬእዮ ንሕነሰ ነአምን ከመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ኅቡራን ህላዌ ወኅቡራን መንግሥት:: ኅቡራን ራእይ ወኅቡራን መለኮት:: ኅቡራን ኀሊና ወኅቡራን ግዕዝ ወሥርዓት:: ወ፩ ሥምረቶሙ ወ፩ ፍትወቶሙ ወ፩ ሕጎሙ ወሥርዓቶሙ ወ፩ ክሂሎቶሙ ወኢይብልምሙ ፫ አማልክተ ከመ አማልክተ አሕዛብ በበሥርዓቶሙ:አላ ይሰምይዎሙ ፩ አምላክ ዘበሥላሴ ወኢይተልዎ ፩ ለ፩ ወካልዑ ለሣልሱ ከመ አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ዘቀደመ ሀልዎ ፩ ቅድመ ፩:: ዮሐ፭÷፴

፲፭ አልቦ ቀዲመ ህላዌ ለአብ እም ወልድ ወቀዲመ ህላዌ ለወልድ እመንፈስ ቅዱስ ኢመጠነ አስተርእዮ መባርቅት ወኢመጠነ ነበስባሰ ቀራንብት::ከመዝ እንዘ ተአምን ወከመዝ እንዘ ትትአመን መሀይምንት እምየ ወእምክሙ ቅድስት ቤተክርስቲያን ታሕተ ጽላሎተ አብ ታጼልል በከመ ጽሑፍ ዘይብል እግዚኦ መኑ የኀድር ውስተ ጽላሎትከ ወመኑ ያጸልል ውስተ ደብረ መቅደስከ ወዲበ መዝራዕተ ወልድ ታሰ ምክ እንዘ ትትፌሣሕ በመርዓዊሃ በከመ ጽሑፍ ዘይብል የማኑ ታሐቅፈኒ ወፀጋሙ ታሕተ ርእስ የ::ወበማኅቶተ ብርሃነ መንፈስቅዱስ ትትመራሕ ውስተ አዕጻዳተ ገነት በከመ ጽሑፍ ዘይብል ወመንፈስከ ቅዱስ ይምርሐኒ በምድረ ጽድቅ:: መዝ፲፬÷፩ መኃ፰÷፫

፲፮ ወእምዝ ታንሶሱ መንገለ ፈለገ ዮርዳኖስ እንዘ ተኀሥሥ ተጠምቆ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ::ወወረደ ውስተ ቀላየ ዮርዳኖስ እንዘ ተኀሥሥ ተጠምቆ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ:: ወወረደ ውስተ ቀላየ ዮርዳኖስ ምዕረ ትጠመቅ በስመ እግዚአብሔር አብ ዘስምዐ ኮነ ለወልዱ በውስተ ምጥማቃት:: ወካዕበመ ትጠመቅ በስመ እግዚአብሔር ወልድ ዘተጠምቀ በእደ ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ:: ወዓዲመ ትሤልስ ተጠምቆ በስመ እግዚአብሔር መንፈስቅዱስ ዘወረደ እምሰማያት ወነበረ ዲቤሁ ለእግዚእ ኢየሱስ በርእየተ ርግብ ዘሥጋ:: ወእምዝ ወፂአ እማየ ዮርዳኖስ ትነሥእ ማኅተመ ዘቅብዐ በለሳን ከመ ትሰመይ አመቶ ለክርስቶስ:እስመ ቅብዐ በለሳንሰ ኃይለ ሃይማኖት ውእቱ: በከመ ይቤሉ ሐዋርያት በትምህርተ ዲድስቅልያ::ወተወልዶሰ እምጥምቀት ይመስል ልደተ

አይችልም እርሱ የደረገውን ያደርጋል እንዲሁ ወልድም በአምሳሉ ያደርጋል አብ ልጁን ይወደዋልና የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል ከዚህም የበለጠ ሥራ ያሳየዋል እናንተ አይታችሁ ታደንቁ ዘንድ እንዳለ ወልድ አብን እንደሚያውቀው ዕወቅ::ስለመንፈስቅዱስም አስቀድመን ነግረናችኋል::ዝንጉዎች ሆይ ከእንግዲህስ ወልድ ከአብ ያንሣል አያየውምም መንፈስቅዱስም ከ ወልድ ያንሣል አያየውምም አትበሉ እኛ ግን አብና ወልድ መንፈስቅዱስም በአካል አንድ እንደሆኑ በመለኮትም አንድ እንደሆኑ በኀሊና አንድ እንደሆኑ በጠባይና በሥርዓትም አንድ እንደሆኑ ፈቃዳቸው አንድ መሻታቸውም አንድ እንደሆነ ሕጋቸውና ሥርዓታቸው አንድ መቻላቸውም አንድ እንደሆነ እናምናለን እንደ አሕዛብ አማልክት በየሥርዓታቸው ሦስት አማልክት አይባሉም በሦስትነት ያሉ አንድ አምላክ ይባላሉ እንጂ አንዱ ከአንዱ በፊት በመኖር እንደ ቀደመ እንደ አብርሃምና እንደ ይስሐቅ እንደ ያዕቆብም አንዱ አንዱን አይከተለውም ሁለተኛውም ሦስተኛውን አይከተለውም:: ዮሐ ፭÷፴

፲፭ የመብረቅን መታየት የሽፋሽፍቶችንም መገለባለጥ ያህል አብ በህልውና ወልድን መቅደም የለውም ወልድም ከመንፈስቅዱስ በህልውና መቅደም የለውም::እንደዚህ ስታምን ደዚህም ስትታመን የታመነች እናቴ እናታችሁም ቅድስት ቤተክርስቲያን በአብ ጥላ ሥር ታርፋለች አቤቱ በጥላህ ውስጥ ማን ያርፋል በመቅደስህም ማን ያድራል ተብሎ እንደተጻፈ ቀኙ ታቅፈኛለች ግራውም ከራሴ በታች ነው የሚል እንደተጻፈ በሙሽራዋ እየተደሰተች በወልድ ክንድ ላይ ትደገፋለች በመንፈስቅዱስ ብርሃን ፋናነት በገነት አፀዶች ውስጥ ትመራለች ቅዱስ መንፈስህ በጽድቅ ጐዳና ይምራኝ የሚል እንደ ተጻፈ:: መዝ፲፬÷፩ መኃ፰÷፫

፲፮ ከዚህም በኋላ በአብና በወልድ በመንፈስቅዱስ ስም መጠመቅን ስትሻ ወደ ዮርዳኖስም ባሕር ወርዳ በመጠመቂያው ውስጥ ስለ ልጁ ምስክር በሆነ በእግዚአብሔር አብ ስም አንድ ጊዜ ትነከራለች ሁለተኛም በዘካርያስ ልጅ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ በእግዚአብሔር ወልድ ስም ትነከራለች ከእንደገናም ከሰማያት ወርዶ በሥጋዊ ርግብ አምሳል በጌታ በኢየሱስ ላይ በተቀመጠ በእግዚአብሔር መንፈስቅዱስ ስም ሦስተኛ ትነከራላች፣ ከዚያም ከዮርዳኖስ ውኃ ወጥታ የክርስቶስ ሴት አገልጋይ ትባል ዘንድ የሜሮን ቅባት ማኅተምም ትቀበላለች የሜሮን ቅባት ሐዋርያት በዲድስቅልያ እንደተናገሩ የሃይማኖት ኃይል ነውና:: በጥምቀት መወለድስ ከድንግል መወለድን ይመስላል ክርስቶስ ከማርያም እንደ ተወለደ ከእርሷም ከተወለደ በኋላ አንቀጸ ሥጋዋ በድንግልናዋ ማኅተም ታትሞ እንደተገኘ

እምድንግል ፡በከመ ክርስቶስ ተወልደ እማርያም ወእምድኅረ ተወልደ እምኔሃ ተረክበ አንቀጸ ሥጋሃ ዕፅወ በማኅተመ ድንግልናሃ ወከማሁ ዘሂ ተወልደ እምከርሠ ጥምቀት ወዒኦ እማይ ኢይትረከብ አሠረ በአቱ ወፀአቱ ውስተ ከርሠ ምጥማቃት፡ በከመ ይቤ በመዝሙር ውስተ ባሕር ፍኖትከ ወአሰርከኒ ውስተ ማይ ብዙኅ ወኢይትዐወቅ አሠርከ፡፡ መዝ፸፯፥፲፱፡፻፵፪፥፲

፲፫ ንግባእ እንከ ኀበ ኀዳገ ነገር ዘቅድስት ቤተክርስቲያን፡፡ወእምዝ ተዐርገ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር እንዘ ታስተዔድም ሑረታቲሃ በአሣእነ ወንጌል ሰሚዓ እምቃለ ጳውሎስ ዘይቤ ተሥኢነክሙ ኃይለ ወንጌል ዘበሰላም፡ ወትወዲ ጌራ ባሕርይ ዲበ ርእሳ ዘውእቱ አክሊለ ሃይማኖት በከመ ዓዲ ነገረ ጳውሎስ እንዘ ይብል ወነሥኡ ጌራ መድኃኒት ወሰይፈ ዘመንፈስ ቅዱስ ዘውእቱ ቃለ እግዚአብሔር፡፡ ወትወዲ ውስተ አጻብዒሃ ህልቀተ ክብር ዘውእቱ ማዕተበ ጸጋ ትእምርተ መድኃኒት፡፡ ኤፌ፮፥፲፯

፲፬ ወእምዝ ትበውእ ውስተ አፀደ መርዓ ኀበ አብርሃም ይረፍቅ ወኀበ ይስሐቅ ተቤዘወ በዝብሐተ በግዕ፡፡ ኀበ ያዕቆብ ርእየ ሰዋስወ ወርቅ እምድር ዘይበጽሕ እስከ ሰማይ፡፡ኀበ መላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ እንተ ይእቲ ሰዋስው፡፡ኀበ ሙሴ ይጸውር ጽላተ ሕግ ወትእዛዝ እለ ይከውና ስምዐ በእንተ ዘለፉ ሆሙ ለደቂቀ እስራኤል፡፡ኀበ መልከጼዴቅ አውጽሐ ኅብስተ ወወይነ ለሥርዓተ ምሥጢር ዘቤተ ክርስቲያን፡ኀበ ዳዊት ይዘፍን ቅድመ ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብል ተንሥእ እግዚኦ ውስተ ዕረፍትከ፡አንተ ወታቦተ መቅደስከ፡፡ ኀበ አሳፍ ይቃኒ ወኀበ ደቂቀ ቆሬ ይሴብሑ በመሰናቅወ መዝሙር፡፡ኀበ ኢሳይያስ የኀሊ ለስብሐተ ፍቁር እንዘ ይብል አኀሊ ለፍቁር ማኅሌተ ዘአፍቀሩ፡፡ኀበ ኤርምያስ ሠጠቀ ኵኵሐ ወአንበረ ውስተ ውሳጢታ ንዋየ ግበሪሃ ለደብተራ ዘመርጡል ወኀተማ ለስጠተ ኵኵሕ ወኮነቶ ከመ ግልወተ ሐጺን ወመራትታ አወፈየ ለፀሐይ፡፡ ኀበ ኤልያስ በልዐ ስባጠ ኅብስተ ዘወሀቦ መልአከ እግዚአብሔር ወሖረ በኃይለ ውእቱ እክል ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ፡፡ወኀበ ዕዝራ ሱቱኤል ሰትየ ጽዋዐ ስብሐት እም እደ ዑራኤል መጻሕፍተ ሕግ ወትእዛዝ እንተ ታሌብዎ ወከብዶ ውስተ እንግድዓሁ ልቡና ወነበረ አፉሁ ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሌተ እንዘ ኢይትጋባእ፡፡ ዘፍ፲፬፥፲፰ ዘጸ፴፩፥፲፰ መዝ፻፴፩፥፰ ፩ነገ፲፱፥፰ ሉቱ፲፫፥፴፰-፵፬

፲፭ ኀበ ዘካርያስ ርእየ አፍራሰ ጸዓድ ዒዳነ ወኵሳኵሳነ፡፡ወኀበ ሕዝቅኤል ርእየ ሠረገላ እሳት፡፡ ኀበ ዳንኤል ርእየ መናብርተ ወእንዘ ይነብር ዲቤሁ ብሉየ መዋዕል ምስለ ወልደ እጓለ እምሕያው፡፡ኀበ ዕንባቆም ርእዮ ለእግዚአብሔር

እንደዚሁ ከጥምቀት ማኅፀን የተወለደ ከውኃ ወጥቶ ወደ መጥመቂያው ውስጥ የመግባቱና የመውጣቱ አሠር አይገኝም በመዝሙር መንገድህ በባሕር ውስጥ ነው ፍለጋህም በብዙ ውኃ ውስጥ ነው ፍለጋህም አይታወቅም እንደ ተባለ :: መዝ፸፯፥፲፱፡፻፵፪፥፲

፲፫ እንግዲህ ወደ ቀረው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ነገር እንመለስ፡ከዚህ በኋላ ከጳውሎስ ቃል በሰላም የወንጌልን ቃል ተጫምታችሁ ያለ ውን ሰምታ በወንጌል ጫማ አካሄዷን አሠማምራ ወደ እግዚአብሔር ቤት ትወጣለች፡፡በራሷም ላይ የዕንቍ ዘውድ ትደፋለች ይኸውም የሃይማኖት አክሊል ነው፡፡ዳግመኛ ጳውሎስ የመድኃኒት ዘውድ የመንፈስቅዱስንም ሰይፍ ተቀበሉ ይኸውም የእግዚአብሔር ቃል ነው እንዳለ ፡፡በጣቶቿም የጸጋ ማዕተብ የመድኃኒት ምልክት የሆነ የክብር ቀለበትን ታደርጋለች፡፡ ኤፌ፮፥፲፯

፲፬ ከዚህም በኋላ አብርሃም ወደ ተቀመጠበት ይስሐቅም በበጉ መታረድ ወደ ተቤዠበት ያዕቆብም ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ የወርቅ መሰላል ወዳየበት በዚያች መሰላል የእግዚአብሔር መላእክት ወደሚወጡበትና ወደ ሚወርዱበት ሙሴም ስለእስራኤል ልጆች ዘለፋ ምስክር የሚሆኑ የሕግና የትእዛዝ ጽላት ወደ ሚሸከምበት፤መልከጼዴቅ ለቤተክርስቲያን ምሥጢር ሥርዓት ኅብስትና ወይን ወዳቀረበበት ዳዊት አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ግባ አንተና የመቅደስህ ታቦት እያለ በእግዚአብሔር የሕግ ታቦት ፊት ወደ ሚዘፍንበት አሳፍ ወደሚቃኝበት የቆሬም ልጆች በመዝሙር መሰንቆዎች ወደሚያመሰግኑበት ኢሳይያስ ለወዳጄ የወደዱትን ዘፈን እዘፍናለሁ ብሎ ለወዳጁ ምስጋና ወደሚዘፍንበት ኤርምያስ አለቱን ሰንጥቆ የአዳራሽ መቅደስ መሥሪያ ገንዘብ በውስጠኛዋ ክፍል ወዳስቀመጠባት የአለቱንም ስንጥቅ ወዳተማት እንደብረት መሸፈኛ የሆነችው መክፈቻዎቿንም ለፀሐይ ወደ ሰጠበት፡ኤልያስ የእግዚአብሔር መልአክ የሰጠውን እንጐቻ ወደበላበት በዚያም እህል ኃይል አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ወደ ተጓዘበት ሱቱኤል ዕዝራ ከዑራኤል እጅ የሕግና የትእዛዝ መጻሕፍትን የምትገልጥለትን የምስጋና ጽዋ ወደ ጠጣበት፤ በደረቱም ልቡና ከበደው ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊትም አፉ ሳይገጠም ሰነበተ፡፡ ዘፍ፲፬፥፲፰ ዘጸ፴፩፥፲፰ መዝ፻፴፩፥፰ ፩ነገ፲፱፥፰ ሉቱ፲፫፥፴፰-፵፬

፲፭ ዘካርያስ ነጫጭና ዥንጉርጉር ፈረሶችን ወዳ አየበት፡፡ሕዝቅኤል የእሳት ሠረገላ ወዳየበት :: ዳንኤል በዘመን የሸመገለው ከሰው ልጅ ጋር ተቀምጦበት መንበርን ወዳየበት ዕንባቆም እግዚአብሔርን በሁለት እንስሳዎቹ መካከል

ማእከለ ክልዔ እንስሳሁ:: ኀበ ኵሎሙ ነቢያት ያደምፁ ሰብከተ በአርጋኖነ ትንቢት::ወኀበ ሕፃናተ ገሊላ ይሴብሑ በቃለ ማኅሌት ዘይመስጥ ኅሊና ወይሰልብ አልባበ ወያጠልል አዕጽምተ:: ወኀበ ጴጥሮስ ተመጠወ መራኁተ ዘመንግሥተ ሰማያት:: ወኀበ ጳውሎስ ተጸውዐ ከመ ይኩን ብርሃነ ለቤተ ክርስቲያን:: ኀበ ዮሐንስ ይኬልሕ ከመ ቃለ ቀርን እንዘ ይሰብክ ምሥጢረ መለኮት:: ወኀበ ኵሎሙ ሐዋርያት ሰተዩ ውኂዘ እሳት በርደተ መንፈስቅዱስ::ወኀበ ይጸዓቁ ማኅበረ መላእክት ለሕዋጼ ምሥዋዒሁ ለእግዚአብሔር ወማኅበረ ሰማዕትኒ እለ ይትቄጸሉ አክሊለ ዘዓስበ ጻማሆሙ ወሕማሞሙ ወማኅበረ ደናግልኒ ወመነኮሳት እለ ይትቄጸሉ አክሊለ ዘዓስበ ጻማሆሙ:: ወእምዝ ይጠባሕ መርዓዊ ለምሳሐ መሀይምናን በውስተ ፒላሳሃ ለመርዓት:: ይርዕድ አብራኪሃ እምነጽሮ ኀርደቱ ወይትሀወከ አማውቲሃ ሶበ ትሬኢ እንዘ ያንጸፈጽፍ ደሙ ውስተ አቅርንተ ምሥዋዕ ትበልዕ ሥጋሁ በፍርሀት ወትሰቲ ደሞ ዘምስለ ረዓድ::ወእምዝ ይረስን ላህበ ሃይማኖቱ ውስተ ልባ ወይፈልሕ ሞገደ ፍቅሩ ውስተ ከርሣ:: ዳን፯፥፱ ዘካ፮፥፩ ማቴ፲፯፥፲፱ ሐዋ፪፥፩ ራእ፲፬፥፩-፭

፲፮ ወይእዜኒ ፈጺመነ ዘለፋሁ ለአርጌንስ ዘይነብብ ጽርፈተ ላዕለ መለኮተ ሥላሴ ንበል ስብሐት ለአብ ለመኰንነ ኵሉ ፍጥረት: ወሰጊድ ለወልድ ለእግዚአ መንግሥት ወነገሥት:አኰቴት ለመንፈስቅዱስ ፈታኔ አልባብ ወኵልያት: ለዓለመ ዓለም አሜን::

፲፯ ተፈጸመ ዘለፋሁ ለአርጌንስ ዘልቡናሁ ጽቡስ ወኅሊናሁ እንሉስ: አጽሐፍክዎ አነ ጊዮርጊስ ወልደ ሕዝበ ጽዮን ቀሲስ: በቃለ አፉየ እንዘ እደርስ: ቀኒዕየ ለሃይማኖተ ሥሉስ : ከመ ኢይኩን ተኀጻጽ ለ፩ እም ፩ መለኮተ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ: ዘሎቱ ይደሉ ስብሐት በባሕር ወበየብስ: በአኀቃል ወአላዳስ: ወሎቱ ይደሉ ስግደት እምኀበ ኵሉ ዘሥጋ ወነፍስ አሜን ወአሜን::

.......... /// ..........

ወዳየበት:ነቢያት ሁላቸው በትንቢት አርጋኖን ስብከትን ወደሚሰሙበት የገሊላም ሕፃናት ኅሊናን በሚመስጥ ልብን በሚስብ አጥንትንም በሚያስመልም የምስጋና ቃል ወደሚያመሰግኑበት ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻዎች ወደተቀበለበት ጳውሎስም ለቤተክርስቲያን ብርሃን ሊሆን ወደተጠራበት ዮሐንስ የመለኮትን ምሥጢር እየሰበከ እንደ ቀንደ መለከት ወደሚጮህበት ሐዋርያትም ሁላቸው በመንፈስቅዱስ መውረድ የእሳትን ፈሳሽ ወደጠጡበት የመላእክት ወገኖች የእግዚአብሔርን መሠዊያ ለመጐብኘት ወደሚተጉበት የድካማቸውንና የመከራቸውን ዋጋ አክሊል የተቀዳጁ የሰማዕታት ወገኖች ወዳሉበት የድካማቸውን ዋጋ አክሊል የተቀዳጁ የደናግልና የመነኮሳት ወገኖች ወዳሉበት ወደ ሠርጉ ሥፍራ ትገባለች::ከዚህም በኋላ ለምእመናን ምሳ ሙሽራው በሙሽሪት አዳራሽ ይታረዳል:: መታረዱን ከማየት የተነሣ ጉልበቷ ይንቀጠቀጣል አንጀቷም ይናወፃል በመሠዊያው ቀንድ ሲንጠፈጠፍ ደሙን ባየች ጊዜ ሥጋውን በፍርሀት ትበላለች ደሙንም በመንቀጥቀጥ ትጠጣለች ከዚያም የሃይማኖት ወላፈን በልቧ ውስጥ ይግላል የፍቅሩም ሞገድ በሆዷ ውስጥ ይፈላል:: ዳን፯፥፱ ዘካ፮፥፩ ማቴ፲፯፥፲፱ ሐዋ፪፥፩ ራእ፲፬፥፩-፭

፲፮ አሁንም በሥላሴ መለኮት ላይ ስድብን የሚናገር የአርጌንስን ተግሣጽ ፈጽመን ለፍጥረታት ሁሉ ገዥ ለአብ ምስጋና ለመንግሥትና ለነገሥታት ጌታ ለወልድም ስግደት ልብንና ኩላሊትን ለሚመረምር ለመንፈስቅዱስ አኰቴት ይገባል እንበል ለዘላለሙ አሜን::

፲፯ ልቡ ደካማ ኅሊናውም የእንስሳ የሆነ የአርጌንስ ተግሣጽ ተፈጸመ::እኔ የቀሲስ ሕዝበጽዮን ልጅ ጊዮርጊስ በአንደበቴ ቃል ደርሼ ከአንድ የአብና የወልድ የመንፈስቅዱስም መለኮት ላይ ማነሥ ለአንዱ እንዳይሆን ሥላሴን ለማመን ቀንቼ አስጻፍኺት:ለርሱ በባሕርና በየብስ በበረሀዎችና በደሴቶች ምስጋና ይገባል ለርሱም ሥጋና ነፍስ ካላቸው ሁሉ ዘንድ ስግደት ይገባል ለዘላለሙ አሜን::

.......... /// ..........